Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# የአራተኛ COVID-19 ክትባት መጠን/doses

ቀን 08 ሀምሌ/July 2022 ዓ.ም

በክረምት ወራት ብዙጊዜ ከመተንፈሻ ቫይረሶች እንደ COVID-19 ያለ በበለጠ ብክለት ይፈጠራል። ከCOVID-19 ቫይረስ በጣም ጥሩ የሆነ መከላከያ ለማቅረብ ተጨማሪ የማበርታቻ፤ ወይም የአራተኛ COVID-19 ክትባት መጠን/dose በCOVID-19 ከሚፈጠር በከባድ የመታመም ችግር ላይ ለሚጋለጡ ሰዎች እንዲወስዱ ይመከራል። ከባድ የበሽታ መቋቋም ሃይላቸው ለተዳከመ ሰዎች፤ ይህ የአምስተኛ COVID-19 ክረምት መጠን/dose ይሆናል።

ለአራተኛ COVID-19 ክትባት መጠን/dose ማግኘት የሚችሉት፤ እርስዎ።

- እድሜዎ 50 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ
- በእድሜ አንጋፋ ወይም በአካለ ጉዳተኛ እንክብካቤ መስጫ መገልገያ ላይ የሚኖሩ ከሆነ

እንዲሁም እድሜያቸው 16 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ለተጨማሪ ማበረታቻ መጠን/dose ክትባት የሚፈቀድላቸው፡

- የበሽታ መቋቋም ሀይልዎ የተዳከመ
- አንዳንድ ነቀርሳዎች ከነበረብዎ ወይም ካለብዎት
- ቀጥታ የበሽታ መቋቋም ድከመት በሽታና ህክምና ካስፈለግዎት
- የማይድን በሽታ ወይም ከባድ በሽታ ካለብዎት፤ ይህም በእርስዎ ሳንባ፤ ጉበት፤ ኩላሊቶች፤ አንጎል ወይም የልብ በሽታ ችግር ካለብዎት
- ህክምና የሚያስፈልገው የስኳር በሽታ ካለብዎት
- አካል ጉዳተኛ ሆነው ጠቃም ወይም የተወሳሰበ ጤና እርዳታ ካስፈለግዎት
- ጤናማ ያልሆነ ውፍረት ወይም ክብደት መቀነስ ካለብዎት ነው።

እድሚያቸው ከ30 እስከ 49 ዓመት ለሆኑት ሰዎች እንደ ምርጫቸው የአራተኛ መጠን/dose ማግኘት ይችላሉ።

ለአራተኛ መጠን/dose ክትባት መውሰድ እንዳለብዎ እርግጠኛ ካልሆኑ ከሀኪምዎ ጋር መነጋገር ነው።

ለአራተኛ የCOVID-19 ክትባት መጠን/vaccine dose ማግኘት የሚችሉት፤ ለመጀመሪያ ማበረታቻ መጠን/dose ወስደው ቢያንስ **3 ወራት** ከሆነ ነው።

የእርስዎን COVID-19 ክትባት እና የኢንፍሉወንዛ ክትባት በተመሳሳይ ጊዜ መውሰድ ይችላሉ።

በቅርቡ በምርመራ ውጤት አወንታዊ የCOVID-19 ቫይረስ ከተገኘብዎት፤ ቀጣዩን የCOVID-19 ክትባት መጠን/dose ከመውሰድዎ በፊት ለ**3 ወራት** እንዲጠብቁ ይመከራል።

ለበለጠ መረጃ በድረገጽ www.health.gov.au ላይ ማየት ወይም ለNational Coronavirus Helpline በስልክ 1800 020 080 አድርጎ መደወል። ለነጻ አስተርጓሚ አገልግሎቶች ቁጥር 8'ን መምረጥ።